## ኢፍቲን

የት/ቤቶችን የተማሪዎች ዩኒፎርም ለብሰው ወደ ት/ቤት ቅጥር ጊቢ በመግባትና ከውጭም በመሆን ረብሻ ለመቀስቀስ ሙከራ ሲያደርጉ ደርሼባቸዋለሁ ያላቸውን 22 ተጠርጣሪዎች ፖሊስ በቁጥጥር ሥር ማዋሉ ተገለፀ፡፡

እነዚህ 22 ተጠርጣሪዎች የትምህርት ቤቶቹ ተማሪዎች ሳይሆኑ ዩኒፎርም በመልበስ በየት/ቤቶቹ ቅጥር ጊቢ ውስጥ ሁከት እንዲቀሰቀስ እንደዚሁም ከአጥር ውጭ ረብሻ እንዲነሳ አቀጣጣይ በመሆን በጥፋት ተግባር ላይ ተሰማርተው እያለ ከአዲስ ከተማ፣ ከምኒልክና ከጥቁር አንበሳ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መያዛቸው ተመልክቷል፡፡

በሁከት ማነሳሳት ተግባር ተጠርጥረው የተያዙት እነዚህ 22 ሰዎች ለፖሊስ በሰጡት ቃል ለእያንዳንዳቸው ሃምሳ ሃምሳ ብር እየተከፈላቸው ወደዚህ ዓይነቱ የጥፋት ተግባር እንዲሰማሩ በአንዳንድ ግለሰቦች የተላኩ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ በዚህ መሠረትም ተጠርጣሪዎቹ ለሁከቱ ተግባር ገንዘቡን የሰጧቸውንና ያሰማሯቸውን ሰዎች ለፖሊስ ጠቁመው በቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ማድረጋቸውን የፖሊስ ምንጮችን ጠቅሶ ኢፍቲን ጋዜጣ ዘግቧል፡፡

## በኢትዮጵያ መንግስት አጠቃላይ በጀት የውጭ ምንጭ ድርሻ

መንግስት ለተለያዩ ተግባራት ሥራ ማስኬጃ ከሚመድበው በጀት በተጨማሪ የውጭ ፋይናንስ በዕርዳታና በብድር መልክ ይገኛል፡፡ በዕርዳታና በብድር ወደ አገር ውስጥ ከሚገባው ገንዘብ ውስጥ ደግሞ ቀደም ሲል በካውንተር ፓርት ፈንድ፤ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ በቀጥታ በጀት ድጋፍ መልክ የሚፈሰው ይገኝበታል፡፡

ቀደም ባሉት ዓመታት በካውንተር ፓርት ፈንድ መልክ ይገኝ የነበረው ዕርዳታና ብድር ለጋሽ መንግስታት በዕቃ መልክ የሚሰጡትና ዕቃው ተሸጦ ገንዘቡ ለትሬዠሪ በመግባት ለመንግስት ወጪ መሸፈኛ ይውል የነበረው ይጠቀሳል፡፡ በዚህ መልክ ወደ አገር ውስጥ ይገባ የነበረው በአመዛኙ ማዳበሪያ እና እህል ሲሆን ይህንንም ድጋፍ ከሚሰጡት ሀገሮች መሀከል የጃፓን፣ የጣሊያንና የፈረንሳይ መንግስታት ይጠቀሳሉ፡፡

ከ1995 በጀት ዓመት ወዲህ ደግሞ ሀገራችን የቀጥታ በጀት ድጋፍን ከተወሰኑ መንግስታትና ከዓለም ባንክ እንዲሁም ከአውሮፓ ህብረትና ከአፍሪካ ልማት ባንክ በማግኘት ላይ ትገኛለች፡፡ እነዚህ አገሮችና መንግስታት የሚሰጡት የቀጥታ በጀት ዕርዳታና ብድር በውጭ ምንዛሪ ወደ አገር ውስጥ የሚገባ በመሆኑ ለመንግስት በጀት መሸፈኛ ከመዋሉም በላይ አገራችን የምትፈልጋቸውን የውጭ ሸቀጦችና አገልግሎቶች ለመግዛት ያገለግላሉ፡፡

ይኸው የበጀት ድጋፍ በአገር ውስጥ ከሚሰበሰበው ገንዘብ ጋር በመደመር በዕቅድ ለተያዙ የፌዴራልና የክልል ወጪዎችን ለመሸፈን ያገለግላል፡፡ ይህ ገንዘብ ከማንኛውም ፕሮጀክት ጋር ያልተያያዘ በመሆኑ መንግስት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው የወጪ ዘርፎች ሊያውለው ይችላል፡፡ ሌላው የዕርዳታና ብድር ዓይነት ደግሞ ልዩ ልዩ ፕሮጀክቶችን ፋይናንስ በማድረግ የሚገኝ ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱ ዕርዳታ አገሪቱ ለምታካሂደው የካፒታል በጀት ወጪ መሸፈኛ የሚውል ሲሆን ድጋፍ ሰጪ መንግስታትና ድርጅቶች በተስማሙበት ስልትና ፍላጐት ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ፋይናንስ ነው፡፡ ይህ ፋይናንስ ከታቀደለት ፕሮጀክት ውጪ ሊፈፀም የማይችል ሲሆን ክፍያውም ቀደም ሲል በተደረጉት ስምምነቶች መሠረት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

በጥቅሉ የአገራችን በጀት በአገር ውስጥ የፋይናንስ ምንጭ ላይ እንዲመሠረት ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡በዚህ መሠረት ባለፉት ዓመታት ከበጀት አፈፃፀሙ በአማካይ 70 በመቶ የሚሆነው ከአገር ውስጥ የፋይናንስ ምንጭ መሸፈኑን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከውጭ የፋይናንስ ምንጭ የቀጥታ በጀት ድጋፍ በአማካይ 13 በመቶ ሲሸፈን የፕሮጀክት ዕርዳታና ብድሩ ደግሞ ወደ 17 በመቶ ይጠጋል፡፡

**የመንግስት አጠቃላይ በጀትና የውጭ የፋይናንስ ምንጭ ድርሻ በመቶኛ ከ1994-1998 ዓ.ም.**

| | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 | 1998 |
|---|---|---|---|---|---|
| የመንግስት በጀት /ከቀረጥና ከቀረጥ ውጭ የሚገኝ ገቢ/ | 64.1 | 70.7 | 72.0 | 71.8 | 71.8 |
| ከውጭ የሚገኝ ቀጥታ የበጀት ድጋፍ | 15.0 | 9.9 | 13.2 | 14.4 | 11.7 |
| - በዕርዳታ | 1.9 | 3.0 | 11.7 | 10.8 | 11.7 |
| - በብድር | 13.2 | 7.0 | 1.5 | 3.6 | 0.0 |
| ከውጭ የሚገኝ የፕሮጀክት ድጋፍ | 20.9 | 19.3 | 14.8 | 13.8 | 16.5 |
| - በዕርዳታ | 6.8 | 7.6 | 5.4 | 7.0 | 9.8 |
| - በብድር | 14.0 | 11.7 | 9.4 | 6.7 | 6.7 |

- *ምንጭ ኢፍቲን የታህሳስ 28 ቀን 1998 ዓ.ም. ዕትም*